“ግብር ለሚገባው ግብር ገብሩ”

ጌታቸው ኃይሌ

የክርስቲያኖቹ መጽሐፍ “ግብር ለሚገባው (ሹም) ግብር ገብሩ” ይላል ። ግብር ለማይገባው እንደወያኔ ላለ ገዢ ግን ግብር ስለማይገባው አንዲት ቀይ ቤሳ አታቅምሱት ማለቱ ነው ። ጊዜ ስለሰጠው ቀምቶ ይወስዳል ። ግን ብዕሬ ስቦኝ ነው እንጂ ለማለት የፈለግሁት እንኳን “አድናቆት ለሚገባቸው የኦሮምኛ ተናጋሪ የጎሳ ፖለቲከኞች አድናቆት ስጧቸው” ለማለት ነበር ።

ታሪኩ እንዲህ ነው ፤ ኢጣልያ ሰሜን ኢትዮጵያን ቆርሳ ወስዳ በቁራሹ ውስጥ ያሉትን የተለያየ ስም ያላቸውን ወረዳና አውራጃዎች ሰብስባ አንድ ራሷን የቻለች ሀገር ለማድረግ “ኤርትራ” የሚል ስም አወጣችለት ። ከ1890 ዓ. እ. ጀምሮ ብዙዎቹ ክፍለ ሀገሮች አንድ ሀገር ሆኑ ። ከኢትዮጵያ የመገንጠል ሐሳብ በውስጣቸው የሠረፀባቸው የዚያ አካባቢ ልጆች በአንድ ስም ለመጠራት አመቻቸው ። ኢጣልያ ያንን አካባቢ ወስዳ አንድ ሀገር እስክታደርገው ድረስ ነዋሪዎቹን ከኢትዮጵያዊነት በቀር “ማን” የሚያደርጋቸው ሌላ ነገር ወይም ምክንያት አልነበራቸውም ። በሀገር ደረጃ ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ በጎሳ ደረጃ በየራሳቸው ስም የሚጠሩና ወደብዙ ጎሳ የሚዘረዘሩ ዘጠኝ ጎሳዎች ናቸው ። አሁንም በዚያው ደረጃ አሉ ። የኢጣልያ አገዛዝ ስማቸው ኢትዮጵያዊ ከመባል ኤርትራዊ ወደመባል ለወጠው እንጂ የውስጥ የጎሳ መታወቂያቸው እንዳለ ነው ። ከኢጣልያ ግዛት ሲወጣና ከኢትዮጵያ ጋር ሲደባለቅ እልል ያለው ሕዝብ ስሙንም ሆነ መገንጠሉን መውደዱን ለማመን ያስቸግራል ። ተደባብሶ ከዚህ ደረሰ እንበል ።

አሁን ተራው የቱለማና የበረይቱማ ልጆች ነው ። <u>አንደኛ</u> ፥ የታሪኩ እውነተኛነት በማንም የታሪክ ሊቅ ሳይረጋገጥ ፥ የበረይቱማና የቦረን ልጆች ኦሮሞ የሚባል አንድ ሕዝብ ሳይሆኑ ፥ “ኦሮሞ የሚባል አንድ ሕዝብ ነን” ብለው ዓለምን አሳመኑ ። ሊደነቁ ይገባቸዋል ። <u>ሁለተኛ</u> ኢጣልያ ከኢትዮጵያ ላይ መሬት ቈርሳ ኤርትራ የምትባል ሀገር እንደፈጠረች ፥ የበረይቱማና የቦረን ልጆችም ፥ ማንም ልብ ሳይለው በወያኔዎች አዋላጅነት ኦሮሚያ የሚባል ሀገር ፈጠሩ ። ተደባብሶ ከዚህ ደረሰ እንበል ። እንግሊዞች ያልሆነላቸው ለነሱ ሆነላቸው ። ሊደነቁ ይገባቸዋል ። ዛሬ ስለ ኦሮሞ ሕዝብና ስለኦሮሚያ ሀገር አፉን ሞልቶ የማይናገር ፥ ጆሮውን ከፍቶ የማይሰማ በቊጥር ነው ። “የቱ ነው የኦሮሞ ሕዝብ?” ብሎ ለሚጠይቅ (የሚጠይቅ ካለ) የሚያሳዩት በኦሮሞ ሕዝብነት ምን ጊዜም <u>**ያልመከቱትን**</u> ኦሮምኛ ተናጋሪዎችን (የበረይቱማንና የቦረንን ጎሳዎችን) አንድ ሕዝብ አድርገው ነው ። ታሪካቸውን እንደምናውቀው ከሆነ ፥ ጎሳዎቹ ከባህል ያለፈ አንድነት የነበራቸው ጊዜ አልነበረም ። የሕዝብ አንድነት ምልክቱ ፥ ለአንድ ጉዳይ (በተለይ ለአንድ ችግር) በአንድነት <u>**መመከቱ**</u> ፥ <u>**አጸፋውን መስጠቱ**</u> ነው ። አንድ ሕዝብ አንድነቱን የሚያሳየው ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳደረገው በአንድነት ሲዘምት ፥ በአንድነት ሲመክት ፥ በአንድነት አጸፋ ሲሰጥ ነው ። አፄ ሠርጸ ድንግል ቱርኮችን ከምድረ ባሕር (ዛሬ ኤርትራ ከምትባለው ሀገር) ያስወጣቸው አንድነት ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ (በተለይ የበረይቱማ ጎሳዎችን) አስሰልፎ ነበር ። አድዋንና ማይጨውንም መጥቀስ ይቻላል ። የበረይቱማና የቦረን ጎሳዎች እንዲህ ዓይነት ታሪክ የላቸውም ። የጋራ ችግር ገጥሟቸው በጋራ አልመከቱም ፤ በጋራ አጸፋ አልሰጡም ። የቱለማና የበረይቱማ

ጎሳዎች ከደቡብ ተነሥተው ማህል ኢትዮጵያን የወረሩት ለከብታቸው ግጦሽ ፍለጋ ስለነበረ ፥ ወረራቸው እንደ አንድ ሕዝብ ሳይሆን እንደ ባላንጣ እርስ በርሳቸው እየተዋጉ ነበረ ።

እርግጥ ፥ የባህል አንድነት በመሠረቱ የሕዝብን አንድነት ያመለክታል ። የበረይቱማና የቦረን ልጆች ቋንቋቸውና ሌላው ባህላቸው ተመሳሳይ ነው ። አንድ ጊዜ አንድ ሕዝብ ቢሆኑ ነው ። አንድ ያልሆነ ሕዝብ ከመነሻው በአንድ ቋንቋ አይናገርም ። ግን ያ የጥንቱ አንድነት በጥንትነት ቀርቷል ። የአዳም ልጆች በአንድ ቋንቋ ይናገሩ ነበር እንደማለት ነው ። በልጂጎችና ፈንሳዮች ፥ አልናኖችና ነምሳዎች ፥ (ጀርመኖችና አውስርቲያዎች) በአንድ ቋንቋ እንደሚናገሩ እንደማለት ነው ። የአሁኖቹ የበረይቱማና የቦረን ጎሳዎች ሁኔታቸው የሱማሌዎችን ሁኔታ አይቶ ማየት ነው ። ከቀረው ከጥንቱ አንድነታቸው ወዲህ አንድነት ነበራቸው ከተባለ በኢትዮጵያዊነትና በኬንያዊነት ነው ። ኤኮኖሚያቸው ከላይ እንደጠቀስኩት ፥ ከብት ማርባት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ፥ የነዚህ እንደ አሸን የሞሉት ጎሳዎቻቸው ታሪክ የአንድ ሕዝብነት ሳይሆን ፥ በግጦሽ መጣላት ነበር ። ለምሳሌ ፥ ወረንሻ መጀመሪያ ከወርድያ ጋር ተስማምቶ ነበር ፤ ወርድያን ከድቶ ፥ ሕዝቡን ፈጅቶ **ከአክቹ** ጋር ሆነ ፤ አክቹን ከድቶ ሕዝቡን ፈጅቶ ወደ **ሊበን** ሄደ ፤ ሊበንን ከድቶ ሕዝቡን ፈጅቶ ወደ **ወሎ** ተጠጋ ፤ ወሎን ከድቶ ፥ ከሊበን ጋር ታረቀ ።

ከደቡብ ኢትዮጵያ እየወጡ ማህል ኢትዮጵያን ሲወሩ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የነበራቸው ጥል ፥ የአርሶ አደሩን ሰብል ጐልቀኍ ወመሳፍርት ለሌለው መንጋችሁ መኖ አድርጋችሁ ሰላማዊውን ሕዝብ አታስርቡት ፤ ቅዱሳት መካናትንም የከብት በረት አታድርጓቸው ስለሚባሉ ነበር ። የከብታቸው ብዛት እንደ አንበጣ ሰብሉን ላስ ያደርገው ነበር ። ነገሥታቱ ቢቸግራቸው አንዳንዶቹን ባዶ ቦታ እየፈለጉ ያሰፍሯቸው ነበር ። አልሆነም ፥ ከአንዱ ጋር ሰላም ሲፈጠር ሌላው ይከዳል ። ከላይ የጠቀስኩት ወረንሻ ሊበንን ከድቶ ከንጉሥ ሱስንዮስ ጋር ተስማምቶ ወለቃ ላይ ቢያሰፍረው የወለቃን ሰዎች ፈጃቸው ።

የጎሳዎቹ ቍጥር በልክና በትክክል አይታወቅም ። አለቃ ታየ ባደረጉት ጥናት እነዚህን መዝግበዋል ፤

የጎሳ አባቶች ፤ ከረዩ ፥ መረዋ ፥ ኢቱ ፥ አክቹ ፥ ወረነሻ ፥ ሁምበና ።

ልጆች ጎሳዎች ፤ ሊበን ፥ ሜጫ ፥ ቱለማ ፥ ወሎ ፥ ጅሌ ፥ አቦ ፥ ሉባ ፥ በላእ ፥ ወርድያ ፥ አሩሲ ፥ ኢቱ ፥ ኡር ፥ አበጢ ፥ ጅሌ ፥ ጅንጉር ፥ ጨፋ ፥ ሰዩ ፥ አቡ ፥ ጫቡ ፥ ይሉ ፥ ጉድሩ ፥ ኩታይ ፥ አሞሩ ፥ ሆሮ ፥ ራያ ፥ አዘቦ ፥ አሸንጌ ፥ ዳጨ ፥ ኮኖ ፥ ቦች ፥ አካኮ ፥ ወቦ ፥ ጭሌ ፥ ሊበን ፥ ሆኮ ፥ ሌቃ ፥ ጨለባ ፥ ወለጋ ፥ ጉማ ፥ ሊሙ ፥ ጅማ ፥ ጌራ ፥ አብቹ ፥ ግምብቹ ፥ ወበሪ ፥ ገላን ፥ ሉሜ ፥ ሜታ ፥ ዋዩ ፥ ጉለሌ ፥ ሰላሌ ፥ አበቲ ፥ ደራ ፥ ቦረና ።

ወያኔዎች የትግራይን ሕዝብ "አማራ በድሎሃል" እያሉ በማሳመንና በማስፈራራት ኢትዮጵያ የትግራይ ጠላት መሆኗን ያመኑ ፥ ለመግደልም ለመሞትም የቈረጡ ብዙ ልጆች መለመሉ ። ሕዝቡንም ፕሮፓጋንዳውን ማመን አለማመኑ ሳይታወቅ ፥ ያመነና አገሩን የከዳ አደረጉት ። የነዚህ ከላይ የዘረዘርኳቸው ጎሳዎች ሁኔታም ተመሳሳይ ነው ። የፖለቲከኞቹ ጥረት ጎሳዎቹ ከራሳቸው ጎሳና ከኢትዮጵያዊነታቸው በቀር አንድ የኦሮሞ ሕዝብ መሆናቸውን ሳያውቁት እንዲቀበሉት ለማድረግ ነው ።

እየቀናቸው ነው ። የበረይቱማና የቦረን ዘር የሆነ ሁሉ የጎሳ ፖለቲከኞች የጠነሰሱለትን መጕንጨት ጀምሯል ። አንዲት ሴት ሙስሊማ ከሆነች "ፊትሽን በሂጃብ መጀቦን አለብሽ" እንደምትባል ማለት ነው ። ማስገደጃው በኃይል ማስጨነቅና በፕሮፓጋንዳ ወጥሮ መያዝ ነው ። ተበድላችኋል ተብለዋል ፤ የሰፈሩበትን መሬት ሰፍረውበትና እየተጠቀሙበት ሳለ ፥ "አልሰፈራችሁበትም ፥ አልተጠቀማችሁበትም ፥ አማራ ወስዶባችሁ መሬት አልባ ሆናችኋል" ተባሉ ። በዓይን ማየት በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፖለቲካ እውነትን ለማመን አልጠቀመምና የተባለውን የሚቀበሉት ቍጥራቸው እየጨመረ የሄደ ይመስላል ።

ከላይ እንደገለጽኩት ፥ መቼም "ኦሮሞ" የሚለው ስም ለሌለ ሕዝብ አልወጣም ። በጎሳ ከመበታተናቸው በፊት እንደ ቋንቋው ከጥንት የተወረሰ ሆኖ የጥንት አገራቸውን ሳይለቁ የተጠሩበት ስም ሊሆን ይችላል ። ማህል ኢትዮጵያን ከወረሱ በኋላ ግን የሚታወቁት በየጎሳቸው ነው ። "<u>ጃዊ</u> የአዘዞን ሕዝብ ሰለበ" ፤ "በ<u>ወርድያ</u> ጦር ምክንያት አገሪቷ ተሸበረች" ፤ "በዚህ ዓመት መጠኑ አርባ ሺ የሚሆን <u>ለበቻ</u> ወደ ትግሬ መጣ" ፤ ወዘተ. የሚል እንጂ አንድም ቦታ "<u>ኦሮሞዎች</u> እንዲህ አደረጉ" የሚል ሰነድ የለንም ። በአንድ ሕዝብነት ስማቸው ታውቆ ቢሆን ኖሮ ሊቃውንቱ ዛሬ በተጠላው ስም ከመጥራት ይልቅ በታወቀው ስም ይጠሯቸው ነበር ። ጎሳዎቹም ኦሮሞ ነን አላሉም ፤ ጸሐፊዎቹም ኦሮሞ አላሏቸውም ። ግን "ኤርትራ" ከሚለው የቅኝ ገዢዎች ካወጡት ስም ይሻላል ፤ አገር በቀል ነው ።

የታሪክን ሂደት ስናይ ፥ ሀገር የሚገነባውም ፥ የሚፈርሰውም በኃይል ስለሆነ ፥ ኦሮሚያን ለመፍጠር የሚካሄደው ድርጊት አዲስ ሊሆንብን አይገባም ። ግን ያለንበት ዘመን የሕዝብ ድምፅ የሚከበርበት ስለሆነ ፥ አባቶቻቸው በጋራ የገነቧት ሀገር (ኢትዮጵያ) የወደፊት ዕጣዋ ሲጣል ፥ እነሱም ኢትዮጵያዊነታቸው ሲገፈፍ ፥ ፈቃዳቸው መጠየቅ ነበረበት ። የማይጠየቁት መልሱ ስለማይጥም መሆኑን በየምርጫ አጋጣሚ አይተነዋል ። ጎሰኝነትን "ዓይንህን ለዐፈር ይዳርገው" ብለውት ነበር ። ግን የሕዝብ ፈቃድ መጠየቅ በዲክታተሮች ዘመን የማይታሰብ ነው ። ዲክታተሮች "የሥልጣን ምንጩ ሕዝብ ነውና ሕዝብ ልቀቁ ብሏችኋል" ሲባሉ ፥ "ዛሬ ማታ ሕይወታችሁ ታልፋለች" የተባሉ ይመስል ፥ ሕይወታቸው እስክታልፍ በእምቢተኝነቱ ይጸናሉ ።

የብዙነት ኃይሎች የአንድነት ኃይሎችን መብት ነጥቀው ትጥቃቸውን አስፈትተው ይገዟቸዋል ፤ ፍላጎታቸው ተጨቁኗል ። አገራቸውንም የጠላት ንብረት አድርገዋታል ። "የአንድነት ኃይሎች" ስንል "ነፍጠኞች አማሮች" የምንል ያስመስሉታል ። "ነፍጠኞች" ቢሉ እውነታቸውን ነው ። "ነፍጥ" ማለት ጠመንጃ ማለት ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት ሠራዊት አገር ያቀናው ፥ ዳር ድምበር ያስከበረው ፥ በነፍጥ እንጂ በአርጩሜና በአለንጋ አይደለም ። ቅጽሉ "ለአማሮች" መሆኑ ግን ስሕተት ነው ፤ የኢትዮጵያን የጦር ሠራዊት ታሪክ ማንበብ ከስሕተት ያድናል--ከስሕተት ለመዳን ለሚፈልግ ማለት ነው ።

ብዙዎች አውራጃዎችን ማጠቃለል የሚወደደውም ሆነ የሚጠላው በዓላማው ነው ። ለአስተዳደርና የሀገሪቱን ኢኮኖሚው ለማዳበር እንዲመች ከሆነ ይደገፋል ፤ ያውም ቢሆን በሕዝብ ፈቃድ ሲፈጸም ነው ። በቋንቋ ማጠቃለል ግን ተንኮልና በደል አለበት ፤ ይጠላል ። ተንኮልና በደልን አጥብቀን መቃወም አለብን ፤ የሠለጠነ ሕዝብ ግዴታና ምልክት ነው ። ተንኮሉ ፥ "አንድ ሕዝብ አይደለንም" ብሎ ለመለያየትና

ኢትዮጵያዊነትን ለማስቀረት ማመቻቸት ነው ። ለዚያ ከፉ ቀን እንዲያመች “ኦሮሚያ” እና “ትግሪያ” ነፍጣቸው በጋለበ ሰፋፊ መሬት ይዘዋል ። በደሉ ፥ ቋንቋው ሌላ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሰብአዊ መብቱ ይወሰድበታል ፤ ወይ ይባረራል ፥ ወይ ማንነቱን እንዲለውጥ ይገደዳል ። “ኦሮሚያ” ውስጥ ያለቁትና በሺ የሚቈጠሩ ተፈናቃዮች በማስተጃነት እንውሰዳቸው ። “ጥፋቱ የኛ አይደለም ፤ የነእገሌ ነው” ለሚሉት ጥፋትን ካንዱ ወደሌላው ማንቀዋለል ዋጋ አንሰጥም ። የጥፋቱ ምንጭ አንድን ሕዝብ  በቋንቋ መከፋፈል ነው ። ዘዴው አለማግባቢያ መሆኑ የሰናኦርን ግምብ በገነቡ ሰዎች ላይ አይተነዋል ።

ማንነትን በተመለከተ በወልቃይ ጸገዴ ሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን ሥቃይ እንመልከት ።

**ለኦሮሞ ታሪክ ጸሐፊዎች** በተለይ ፤  የኦሮሞዎች ታሪክ የተፈጸመው በኢትዮጵያ ምድር ላይ ስለሆነ ፥ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው ። የቦረንና የበረይቱማ ልጆች ማህል ኢትዮጵያን እንዴት እንደያዙ ሊቃውንቱ ብዙ ጽፈዋል ። ታሪካችን ስለሆነ እንቀበለዋለን ። የደናቁርቱን ጫጫታ ንቃችሁ የሊቃውንቱን መዛግብት በገለልተኝነት መርምሩና  ታሪካችንን አስተምሩን ። ትልቅ ሕዝብ ታሪክ አንብቦ የሚቆጨው ፥ “ምነው በዚያን ጊዜ እንዲህ በሆነ ነበር” ብሎ ነው እንጂ ፥ “በዚያን ጊዜ እንዲህ ከሆነ ዛሬ መበቀል አለብን” ብሎ በቀል ለማንሣት አይደለም ። በደል ያልደረሰበት የለም ። በደል ያላደረሰ አባት ያለው የለም ።

**ለአማርኛ ተናጋሪዎች** ፤ ጀግና “ተበደልኩ” እያለ እሮሮ አያሰማም ።